# እርምት ለሙሴ ፊልምና ለደራሲው ብርሃነ ንጉሴ ከኣስገደ ገ/ስላሴ –መቀሌ

የህወሓት ኢህኣዴግ ታሪክ ገንዘብ ለማግኘት ኣሁን ላሉ የህወሓት ኢህኣዴግ መሪዎች በማሞገስና በማግነን እንደየስራ መስክና ገንዘብ ለማግኘት ሃብት እንደመካበት ተቆጥሯል።
ኣንድ ኣንድ የህወሓት ታሪክ እናውቃለን ፀሓፊዎች ነን የሚሉ የህወሓተ ታጋዮችና ወጣት ሲቪል ፀሓፊዎቸ ፣ሙሁራኖች የህወሓት የ17 ኣመት የትግል ጉዞና ከዚያም በኋላ የተሰሩ ገድላዊ ስራዎች ኣስመልክቶ መጻፍ ከጀመሩ ኣመታት ኣስቆጥሯል ።

በተጨማሪ ከህወሓት ታሪክ ቀንጨብ እያደረጉ በፊልም መስራትም ተጀምሯል።ከነዛ ከተፃፉት መጽሻፍቶች ውስጥ የህወሓት መሪዎች የሚወዷቸውና የማይወዷቸው ኣሉ እነሱም መንነታቸው ለመግለፅ

ሀ.ህወሓት የሚዎዳቸው መፃሕፍት

ሀ.1ጥልመት የሚል መፅሓፍ በደጉተር ሰለሞን ዕንቋይ የሻዕብያ ክዳትን የሚገልጽ ግን ደግሞ ውስጣዊ ይዘቱ ለሻዕብያ የሚሸልም መፅሓፍ ተፅፏል።

ሀ.2የትግራይ ህዝብና የትምክህተኞች ሴራ የሚል መፅሓፍ በመምህር ገብረኪዳን ደስታ የተፃፈ ህዝብን የሚነጣጥል መፅሓፍ ።

ሀ.3ባድመ እንደ ምክንያት በኮነሬል ተወልደ ገብረተንሳይ ብዙ ጉድለቶች ይዘት ያለውና በኤርትራ ጦርነት ትልቅ ሚና የነበራቸው መሪዎች ስራቸው የሚደመስስና ላልነበሩ መሪዎች የሚሾም መፅሓፍ።

ሀ.4ፅናት የሚባል የህወሓትና የትግራይ ህዝብ ታሪክ ለኣቶ ስዩም መስፍን ብቻ ያሸከመ በወጣት ሃይላይ ሓድጉ የተፃፈ ገንዘብን ለማግኘት ማእከል ያደረገ ብዙ የተነገረለት

ሀ.5መርትዖ የሚል መፅሓፍ በሸፋኑ የሰው ምላስ መቀስ የሚቆርጥ  ያለው ኣትፃፍም ኣትናገሩም የሚል በወለገብርኤል ታደሰ የተፃፈ ገንዘብ ለማግኘትና መሪዎች ለማስደሰት የተፃፈ መፅሓፉ በህዝብ ምንም ተቀባይነት የሌለው።

ሀ.6ገላህቲ ሰጊ በሙሉ ጌታ ደባልቀው የተፃፈ መሪዎችን ኣመጉስ ክብርና ገንዘብ ለማግኘት ኣላማ ያለው እጅጉን ኣድርባይ መፅሓፍ

ሀ.7መለስና የህወሓት ጉዞ የሚል እጅግ ብዙ ስህተት ያለውና ኣሁን በስልጣን ያሉ መሪዎች የሚያጎላ ለኣንድ ኣንድን የራሳቸው ያልሆነ ታሪክ የሚሸልም ገንዘብ ለማግኘት ኣላማ ያለው ብዙ ታሪክ የደመሰሰና ያደናገረ መፅሓፍ በኮነሬል እያሱ መንገሻ የተፃፈ በብዙሃን መገናኛ ለወራት ያህል ብዙ  መስታወቅያ የተሰራለትና የተባለለት።

እነዚ ከላይ የተዘረዘሩ መፅሓፍቶች ሁሉም መፅሓፍቶች በኤፈርት ድርጅት የመንግስት መስራቤቶች ክልሉች ወረዳዎች በሚልዮን የሚቆጠር ገንዘብ ወጥቶላቸው የታተሙ ናቸው።ኣንድ ኣንዶችም በዱባይ ታትመው የመጡ ናቸው።የነዚህ መፅሓፍቶች ውስጣዊ ይዞትና ሃቅነት ብዙ ኣንባቢዎች ኣላስደሰተም ለህወሓት ኢህኣዴግ ኣባላትም ጭምር ኣላስደሰተም ምክንያቱም የብዙሃኑ ህዝቦችና ታጋዮች ታሪክ ስለሚዘርፍ ስለሚያበላሽ።

ሌላ ለነዚህ መፅሓፍቶች ለመመረቅ እንደሂልተንና ሸራተን ኣዳራሽ እየተሰጣቸው እንደዚሁም በክልሎች በሓወልት ሰማእታት በዩኒቨርሲቶች ኣዳራሾች እየተመረቁ ናቸው።ከኣገራችን ርእሰብሄር ጀምሮ እስከ ክልል መሪዎች በምርቃን መፅሓፍት የተጠመዱበት ወቅት ነበር።

በሚድያ ሽፋንም በሚመለከት የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ጣብያዎች ድምፅ ወያኔ ትግራይ፣ሬድዮ ፋና፣ኤፍ ኤም መቀሌ ወዘተ. ለሳምንታት ለወራት የማስታወቅያ ሽፋን ተሰጡታቿል።

በገበያ በኩልም የህወሓት በኤፈርት ስር የሚገኙ ተቋማት 25000 ሰራተኛ በላይ ለመንግስት ሰራተኞች ለመከላከያ ሰራዊት ትምህርት ቤቶች ለህወሓት ኢህኣዴግ ኣባላት እንዲሸጡ ተደርጓል።የትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮም በብዛት በመግዛት ለትምህርት ቤቶች ያካፍላል።የመቀሌ ዩኒቨርሲቲም ለኣንድ ኣንድ ፀሓፊዎች የስኮላር ሽልማት ሰጥቷል።በግቢም ላይብረሪም እንዲገቡ ይደረጋል እነዚ መፅሓፍቶች በተለይ ፅናትና ጥልመት የህወሓት ታሪክ ለመፃፍ እንደ መነሻ በማድረግ በታሪክና ቋንቋ ፋካሊቲ እንዲፃፉ 43 ሚልዮን በጀት ፀድቆላቸው በ5 ኣመት ውስጥ እንድፃፍ ተደርጓል።
ለ.በህወሓት ተቀባይነት የሌላቸው መፅሓፍቶች ግን ደግሞ በኣንባብያን በህወሓት ታጋዮችና መሪዎቸ ሳይቀር በህዝብ ተቀባይነት ያላቸው ለህትመት ስፖንሰር የማያገኙ በገንዘብ ድሆች ግነ በይዞታቸው ሃብታሞች  በብዙሃን መገናኛ የማይንገርላቸው የታፈኑ።
  1.ጋህድ ኣንድ በህወሓትና በህዝባዊ ግንባር ሐርነት ኤርትራ የነበረ ግንኙነት ከጥዋቱ ጀምሮ በጌታና በሎሌ የተመሰረተ ነበር የሚል በትግርኛና በኣማርኛ በኣቶ ኣስገደ ገ/ስላሴ ወ/ሚካሰኤል በህወሓት መስራች የተፃፈ
  2.ጋህድ 2 የህወሓት ኣመሰራረት፣ግንባታው፣እድገቱ ከ1968 ዓ.ም እስከ 1977 ዓ.ም በ22 ምእራፋት በትግርኛ ተፅፎ በኣማርኛ በቅርብ ግዜ ታትሞ ይወጣል።
  3.ጋህዲ 3 ከጋህዲ 2 የቀጠለው ከ1977 ዓ.ም ግማሽ ኣመት እስከ 1996 ዓ.ም ያለው ግዜ የሚገልፅ በ29 ምዕራፋት የተፃፈ።እነዚህ ጋህዲ 2 ና 3 በኣንባቢያን ብዙ ተቀባይነት ያላቸው በህወሓት ኢህኣዴግ ኣባላትና ኣብዛኞዎቹ መሪዎች ጭምር ተደብቀው የሚያነቡት።
  4.ክስታይ የሚል ልብወለድ መፅሓፍ በጋዜጠኛና ደራሲ ግርማይ ጌብሩ የተፃፈ በህዝብ እጅግ ተቀባይነት ያገኘ ግን ለህወሓት መሪዎች ያላሰደሰተ መፃፍ በኣገራችን ስላለው ስርኣት በትክክል ስለሚገልፅ።
  5.ማፍያዶ ማለፍያ የሚል መድብለ ግጥም በኣለማዮህ ገዛህይ የተፃፈ ታሪክ ኣዘልና ኣሁን ያለው የስርኣቱ ሁኔታ የሚገልፅ።
  6.ፍትሕና ዳኝነት በኢትዮጵያ በኣሁን ግዜ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ የሚተነትን በኣቶ ስየ ኣብርሃ የተፃፈ በኣንባብያን ብዙ ተቀባይነት ያገኘ።
እነዚህ መፅሓፍቶች በምርቃቸው የክልላችን መሪዎች የታወቁ ሰዎቸ የታሪክና የፖለቲካ ተመራማሪዎች ብዙሃን መገናኛ ተጠርተው ኣብዛኛወፖቹ ሰግተው በመድረኩ ለመገኘት ፍቃደኞች ኣልሆኑም።በተለይ ብዙሃን መገናኛ ስለዚህ 6 መፅሓፍቶች ኣንድም ደቂቃ ለማስተዋወቅ ተንፈስ ኣላሉም።በኣንፃሩ ለነዚህ መፅሓፍቶች ጎንለጎን በማሸማጠጥ እንዲጠሉ ያደርጋሉ።በተለይ ለጋህድ መፅሓፍቶች በኣንድ በኩል በውስጡ ካለው ነጥብ ቀንጨብ እያደረጉ ለህወሓት ቅስቀሳ ይጠቀሙበታል።በሌላ በኩል በተለይ ለጋህድ ኣንድ ድምፅ ወያኔ እንደ ትልቅ ፕሮግራም ይዞ እሁድ እሁድ ለ2 ወር ያህል ኣንፃር ጋህድ ግዜውን እያቃጠለ ነው።ግን ያመጣ ፋይዳ የለም የበለጠ ያላወቀ ሰው ጋህድ ኣንድ የት ኣለ እያለ ሊያነብ ይፈልጋል።

በገበያ በኩል በሽሬ ከተማ ፍፁም በርሄ መፃሕፍት መደብር ሰውየው ለምን ፀረ–ወያኔ መፅሓፍት ትሸጣለህ  ተብሎ የቀበሌ ህዝብ በተሰበሰበበት ተወቅሷል ተገልሷልም።

በሌላ መፃሕፍት ቤቶች በአክሱም በአዲግራት በመቀሌ በማይ ጨው የማይታወቁ ሰዎች ጋህድ መፅሓፍቶች ለምን ትሸጣላችሁ ተብሏል።
በአዲስ አበባም ለመፅሓፍ አዟሪዎች የማይታወቁ ሰዎች ለአዟሪዎች ያስፈራሩዋችኋል።
ትምህርት ቢሮ ክልል ትግራይ መፅሓፍቶች እንዲገዙ ጠይቀናቸው የናሙና መፅሓፍቶች ሰጠናቸው መልስ ሊሰጡ አልቻሉም።ለነዛ በህወሓት መሪዎች ተፈላጊዎች የሆኑ ግን በየአመቱ በሚልዮን የሚቆጠረ በእርዳታ የመጣ ገንዘብ ይገዟችኋል።ስለዚህ ስለ ህወሓትና ሌሎች የሚፃፉ መፅሓፍቶች በህወሓት አይን የቤትና ዳር ልጆች ናቸው።በአሁኑ በህወሓት መሪዎች ፍላጎትና አስተሳሰብ የማይፃፉ መፃህፍት ቦታ የላቸውም።ለሁሉም ግን ትእዝብቱና አስተያየት ለአንባብያንና ለህዝብ ልተወውና አፈናውስ እስከመቼ ነው የሚቀጥለው?
ሐ.ስለ ህወሓት ታሪክ ፊልም የተሰሩ አስገራሚና አከራካሪ የሆኑ ፊለሞች
1.አግአዚ ኦፐሬሽን በሚመለከት የተሰራ ፊልሙ የተሰራ በሁለት ቡድን የተሰራ ነበር።ይህ ፊልም፡
ሀ.በሃይለ አያልነህና በብርሃኑ አባዲ በመፅሓፍና በፊልም ተሰርቷል።ያ መፅሓፍና ፊልም በመሰረቱ ጥሩ ተነሳሽነት ማድረጋቸው የሚመሰገኑ ቢሆንም በመፅሓፉ ይሁን በፊልሙ በኦፐሬሽኑ ወሳኝ አስተዋፅኦ የነበራቸው ወታደራዊ መሪዎች ያገለለ በአጠቃላይ ፊልሙ አሁን በስልጣን ላሉት የህወሓት መሪዎች በቦታው ያልነበሩ ለማስደሰትና ገንዘብ ለመካበት አላማ የነበረው መሆኑ ፊልሙን ያዩ ብዙ ሰዎች ሂስ አድርገውታል።
ለ.እዚሁ የአግአዚ ኦፐሬሽን ጥላሁን ታፈረ በኦፐሬሽኑ ወቅት ኦፐሬሽኑን በበላይነት ይመሩ ከነበሩ ሰዎች ሬድዮ መገኛና ሆኖ ሲሰራ የነበረ የሰራው ፊልም የተሻለ እንደነበረና ሁለቱ ቡድኖች ተወዛግበው በመሃል ገብተው አስታርቋል።ታሪኩ ግን እስከ አሁን እንደተበላሸ ነው።ያ የተሰራው ፊልም በትክክል በጥናትና ለሃቅ ተብሎ የተሰራ ስላልነበረ
የተከበራችሁ አንባብያን የህወሓት ድርጅት በዛ የ17 ኣመት ትግል በጣም ብዙና ላለውና ለመጭው ትውልድ በበጎም በመጥፎም ጥሩ ልምድና ተሞክሮ ሊሆኑ የሚችሉ ስራዎችና ታሪኮች ሰርቷል በትክክል ታሪክ ተመራማሪዎች ቢፅፉት ለአገራችን ትልቅ ቅርስ ይሆን ነበር።ዋና ችግሩ ግን ህወሓት ኢህኣዴግ በተለይ ኣሁን ያሉ መሪዎችና ካድሬዎች ከነሱ አስተሳሰብ ውጭ ሊፃፍና ሊሰነድ አይፈልጉም።ምክንያቱም የህወሓት ታሪክ ነፃ በሆኑ ተመራማሪዎቸ ከተፃፈ ባለ ታሪክ ማነው የሚል መልስ ስለሚያገኝ ሃቁን ግልፅ ስለሚሆን።
እስከ ኣሁን የገለፅኩት የህወሓትን ታሪክ መፅሓፍት መፃፍ በሚመለከት ልተነትን የተገደድኩት ያለ ኣንዳች ምክንያት ኣይደለም።በአሁኑ ግዜ ሙሴ ፊልም የሚባል አርእስት ያለው ፊልም ከደደቢት ሆሊውድ ተሰርቶና ተቀናብሮ በአገራችን ብሄራዊ ቲያትር በተከበሩ ፕሬዚዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስና የህወሓት ኢህኣዴግ ከፍተኛ ባለስልጣኖች እና ከፍተኛ መኮንኖች ባለሌላ ማኣርጎች ባሉበት ተመርቆ በለጋሶች 300.000 በተከበሩ ፕሪዝንዳት ግርማ ወ/ ጎርጊዩስ 10.000ብር ተሸልመዋል፡፡ ይህ ፊልም በመቀሌም መጥቶ መጀመርያ በቦስተን ሲኒማ ቤት በኣቶ ቴድሮስ ሃጎስ አና ሌሎች ባለስልጣኖች ተገምግሞ ይበል ተብሎለታል ተገምግሞ ካበቃ በኋላ ኣዲስ ኣበባ ከተመረቀ በኋላ በየካቲት 11/6/2003ዓ.ም የህውሃትን 36ኛ ዓመት የትግል ጊዜ በኣል ሲከበር እንደገፀበረከት በዚሁ ቀን 8 ሰዓት ጀምሮ እስከ 12 ሰዓት በሃወልት ሰማእታት ተመርቋል በምረቃው ኣብዛኛው የህውሓት ኣባልና ካድሬ የበዛበት ሆኖ የተወሰኑ የመቀሌ ነዋሪዎች እና ነጋዴዎች ነበሩ፡፡
በዚሁ የተሰራ ፊልም በተለይ ትኩረት ልሰጠው የተገደድኩ እኔ ራሴ በኦፐሬሽኑ ስለነበረኩና ስለኦፐሬሽኑ በሚመለከት ጋህድ 2ትን ለመፃፍ ከ15 ዓመት ጀምሬ የፃፍኩትና በ2000ዓ.ም መፅሃፍ ሆኖ ታትሞ ወጥቶ ሁሉም ነገር ሃቁን ግልፅ ኣድርጎ የሚገለፅ ስለነበረ ህዝብ ኣንብቦት በትክክል በታሪኩ የኮራ ብዙ ነበረ ሃቁን መድረክ ወጥቶ በመጋለጡ ጥቂት ያልተደሰቱ ሰዎች ካልሆኑ በስተቀር ሁሉም ተደስቶበታል፡፡ ስለሆነ ወደ ፊልሙ ማንነትና ጠንካራና ደካማ ጎኑ ለመግለፅ በሚቀጥለው አርእስት ተከታተሉኝ፡፡

**ሙሴ ፊልም**

ምንም እንኳን ይሄ ፊልም በዘበነ ህውሓት ኢሃደግ ትንሽ ሃቅን የሚያንፀባርቅ የተሻለ ኣቅጣጫና ሃቅ ያተኮረ ቢመስልም በማወቅ ሆነ ባለማወቅ በጣም ብዙ ስህተቶች የተጫነው ስለሆነ ይህ ፊልም ትኩረት ተሰጥቶበት መስተካከል ሊደረግለት ይገባል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ያሉ ስለፊልም ጠንካራና ደካማ ነጥቦችን በትክክል ታይተው ደግሞ መስተካከል ያለባቸው ናቸው፡፡

የተከበራችሁ ኣንባብያን ይህ ፊልም በድጋሜ ታይቶ መሰራት ኣለበት ስል ያለኣንዳች ምክንያት ኣይደለም ስለዚ ፊልም ከመጀመርያ ጀምሮ እስከ መጨረሻ ስለነበርኩ ሁኔታው በትክክል ስለማውቀው ኣሁን ፊልሙ ሳይ ታሪኩ እጅግ ተበላሽቶ ስላየሁት ይህ ፊልም ኣሁን ባለው ወደ ህዝብ ከሚቀርብ ይልቅ ግዜ ተሰጥቶት ሙያተኞችና ዜጎች ድጋፍ ኣድርገውበት ለትውልድ መልካም ትምህርት ይሰጣል ብየ ስለማምን ነው፡፡ እንግድያዉስ ስለ ሙሴ ፊልም ያለኝ ኣስተያየት መጀመርያ ጠንካራ ጎኑን በዝርዝር ኣስቀምጣለው በሁለተኛ ደረጃ ደካማ ጎኖችን እዘረዝራለው ለኣንባብያን እና ፊልሙ ለሚጠብቁ ግልፅ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡

**ሀ. የሙሴ ፊልም ጠንካራ ጎኖች**

1. እንደ ብርሃነ ፣ንጉሴ እና ሌሎች ወጣቶች የህውሓት ታሪክ በፊልም ሰርተን ስእላዊ በሆነ መንገድ ለትውልድ እንስተላልፋለን በለው ተነሳሽነታቸውን በጣም ማበረታት ተገቢ ይሆናል፡፡
2. የተሰራው ፊልም ወደ ሃቅነት የተጠጋ መሆኑ
3. ያየተሰራ ፊልም ፅናትና መራራ ትግልን ለማያውቁት ኣዲስ የወጣት ትውልድ ፊልሙን በማየት ችግርን እንዴት እንደሚታለፍ ትምህርትን ይሰጣል
4. የፊልሙ ተመልካች ብዙ ነገሮች ሃቅና ውሸት ሊታዘብ ኣድርጎታል
5. እነዛ የፊልሙን ተዋናይ ምንም እንኳን ገፀ ባህሪያቸው የማይመሳሰል ቢሆንም ጥረታቸው ግን ማመስገን ያለባቸው ወጣቶች ናቸው፡፡
6. ፊልሙ ተያዣነት የሌለው ቢሆንም ኣልፎ ኣልፎ የተቆረራጡ ነገሮች ጠቁሟል ያልነበረ ሰው ግን ሊረዳው ኣይችልም ግልፅነት ያስፈልገዋል፡፡የሙሴና የስዩም ገፀባህርያት ጥሩ ነው ይመስላል።እንቅስቃሴያቸው ለመያዝ ግን ብዙ ስልጠና ያስፈልገዋል።የሙሴ ኣያያዝ ፊልሙ ያንፀባርቃል ቴክኒክ ብቻ ይጎድለዋል እንጂ።
7. ሙሴ ለማውጣት ስሑል የያዘው ቡድን ያጋጠሙ ችግሮች ትክክል መሆኑ ያሳያል የትግሉ መራራነት ለትውልድ ያስተምራል።

**ደካማ ጎኑ**

ያ ፊልም (ድራማ) ወደ ደደቢት የተሰማሩ 11 ታጋዮችና ኋላ የተከተሏቸው እንቅስቃሴ ሳያጎላ ጉንበት መጨረሻ በኤርትራ 4 ወር ሙሉ ያለወተዳራዊ ስልጠና ተቀምጦ በሁለት ሳምንት ሞቅሞቅ ወታደራዊ ስልጠና ወስደው ለመጡ ያጎላል፡፡

ደደቢት በኣስገደና ሌሎች ምሁራኖች በጋ ሙሉ ሲሰጥ የነበረ ወታደራዊ እና ፖለቲካዊ ስልጠናዎች ኣልጠቀሰም እንደቁምነገር ኣላዩትም ዋና የፊልሙ ኣስኳል ግን እሱ ነበር፡፡

በዛ ግዜ የነበረ የታጋዮች ባህሪ በዛ ፊልም ያለ ጫጫታና የዱርየ የሚመስል እንቅስቃሴ ኣልነበረም በደንብ የታነፀ የደፈጣ ተዋጊ ዲሲፕሊን ነበረው፡፡

ኣለባበስ በነዛ የፊልም ተዋናዮች ይታይ የነበረ ኣይደለም የኣንዕላ ኣለባበስ የጉዞ ዲሲፕሊን በጥላ ስር ቁጭ ብለው ሲጫወቱ ቀስ ብለው ሚናገሩ እንጂ ጫጫታና ጭፈራ የሚባል ኣልነበረም፡፡ያ የሚታየው ጭፈራ ከ 1972ዓ.ም በኋላ በየማሰልጠኛው ጣብያ የሚደረግ የነበረ ድርጊት ነው፡፡

ወታደራዊ ኣሰለጣጠን ያሳዩን ኣይነት ኣልነበረም፡፡ ኣስልጠኞቹ እነማን እንደነበሩ ኣይታወቅም መጀመርያ በደደቢት የቆዩ ከተገናኙበት ግዜ በኋላ የሚያሰየን ግን ደደቢት ለቆዩ ፍፁም ትኩረት ኣልሰጠም፡፡

ፊልሙ ኣልፎ ኣልፎ ነገሮች የሚያሳይ ቢሆን እንኳን ላልነበረ ሰው በትክክል ሊረዳው ኣይችልም፡፡ ገሰሰ ኣየለ ከደደቢት ወደ ለሌላ ወረዳዎች ኣንወጣም የሚል ስሜትም ንግግርም ኣልነበረውም

ለዚህም መረጋገጫ ኤርትራ የተላኩት በዛው በሄዱበት ቀርተዋል ወይም ኣደጋ ደርሷቸዋል በሚል ተስፋ በመቁረጥ ደደቢት ላይ ጫካ ውስጥ ተደብቀን ኣንቆይም በሞሆኑ እንቅስቃሴያችን ወደ መሃል ትግራይ በማስፋት ከሽሬ እስከ ኣድዋ ተንቤን በርሃዎች እየተንቀሳቀስን ህዝብ እያስተማርን አቅማችን የሚፈቅደው ወታደራዊ እና ፖለቲካዊ ስራዎች እየሰራን የትጥቅና የገንዘብ ችግራችን እንፈታለን ተብለው እቅድ ወጥቶለት እንቅስቃሴ ተጀምሮ ከደደቢት ወደ ምስራቅ 150ኪ/ሜ ተጉዘን ሽሬ ኣልፈን ዛና የሚባለው በወቅቱ የኣክሱም ኣስተዳደር ደርሰን እዛው እንደደረስን ኤርትራ የነበረው ቡድን ባልታሰበ ሁኔታ በህርምም ቀላቅልን ድንገት ደረሰ፡፡

በዛን ግዜ ሁለቱ ቡድን ከተገናኙ በኋላ ተነጋግሮ ደደቢት የቆዩት ይዘውት የነበሩ እቅድ ለጊዜው እንዲቆይና ሁለቱ ቡዱኖች ወደ ደደቢት ተመልሰው እንደኣዲስ ስልጠና ወስደው ወደ መላው ትግራይ እንዲቀሳቀሱ ወሰኑ፡፡ በዛን ገዜ ስሑል ምንም ተቃውሞ ኣልነበረውም ለምን ይህ ጉዳይ እንደተነሳ ግልፅ ኣይደለም ስም ማጥፋትም ነው፡፡ ታሪኩም ማበላሸት ነው፡፡ በታሪኩ በቦታው የነበርንም ኣናውቀውም ተነግሮውም ኣያውቁም፡፡ በቦታው ከነበርን ኣቶ መለስ ኣቶ ኣባይ ኣቶ ስብሓት ኣቶ ስየ ኣምባሳደር ኣውዓሎም ደ/ር ኣረጋዊና ደ/ር ግደይ ደ/ር ካሕሳይ በርሀ ኣስገደ ገ/ስላሴ ኣለን እንግዲህ ስለሃቁን እንመስክር ለምንድነው የገሰሰው ኣየለና የ ኣከባቢው ታጋዮች ታሪክ ለመበላሸት ጥረት የሚደረገው ቢያንስ እኮ ያ ኣካባቢ ህውሓት ከተፈጠረበት እስከ ደርግ መደምሰስ ህውሓት የስምሪት ማእከል ሆኖ ያገለገለ፡፡ በታስትፎም ለልጆቹ ንብረቱ ጭራሽ ያጣ ህዝብ ነው፡፡

ኣቶ ስብሃት ነጋና ኣለማዮ ኣየለ (ድራር) ይዘዋቸው የነበሩ የቀውስ ኣላማዎች በትክክል ኣልተገለፁም፡፡

1. ከሽሬ ኣከባቢ የታገሉ ታጋዮች ቀውስ የፈጠሩ ኣልነበሩም በፊልሙ ግን ከሽሬ የተሰለፉ ታጋዩች ቀውስ ፈጣሪዎች ከደደቢት ሊወጡ የማይፈልጉ ገሰሰው ኣየለና ወንድሙ ብርሀነ ኣየለ ቀውሲ ፈጣሪዎች የሰሩት ሴራ ያውቁ እንደነበሩ ያሳያል ይህ ትክክል ኣልነበረም፡፡ ምክንያቱም በዛን ግዜ ከነበርነው ታጋዮች 80% የዛን ኣውራጃ ታጋዮች ነበሩ፡፡
2. የ ቀውሱ ዋና ተዋናይ ስብሓት ነጋ የህዝቡ ባህል ግምት ያላስገባ የድርጅቱ መመሰረት የት ይሁን የሚል በጥናት የተወሰነ ኣከባቢያዊነት ኣውራጃዊነት በሚፈጥረው መንገድ በስሁል ኣንጠራም ስሁል ወደ ማይታወቅበት እንሂድ ከንግዲህ ከሽሬ ኣከባቢ ታጋዮች ኣንቀበል ከሌላ ኣውራጃዎች ታጋዮች እንሳብ የሚል ኣንጃ በመፍጠር ሲፈፅመው የነበረው ወንጀል ኣልነሳም ብቻ ሳይሆን ኣልተገለፀም እዚ ላይ ፊልሙ ኣድርባይ እና ጌታ ኣዳሪ ያስብለዋል፡፡ በቀውሱ ፈጠራ የሙሁራኖችን ብዱን ኣያስቀምጥም፡፡ ሌላ እነዛ ቀውስ ፈጣሪዎች ለሙሴ እንግደል ኣላሉም ሙሴ ቢቀር ከሻእብያ ጋር ያገናኙናል በመለስና በረዘነም በኛ ላይ መጥፎ ኣመለካከት ስለሌላቸው እንተዋቸው ብለዋል፡፡ በፊልሙ መለስ ንቁ ስለሆነ ያስተምረናል ኣላሉም እዚ ላይ ፊልሙ የኣይን ተገዢነት ኣሳይቷል፡፡ በቀውሱ ግዜም መለስ ታሞ ስለነበረ ያለ መለስ ወክሎ የሚናገር የነበረ ውሸት ነው፡፡ የድርጅቱ ሊቀ መንበር ገሰሰ ኣየለ እያለ በጊዜው ግን ፊልሙ እንደሚያሳየው ሙሴ መሪ እንደነበረነና ለ ሙሴ ከፍ ኣድርጎ ለገሰሰው ኣየለ ዝቅ የሚያደርግ ነው፡፡ፊልሙ በዛን ግዜ ጥሩ ኣስተዋፅኦ የነበራቸው እንደነ ግደይ ዘርኣፅዮን ኣረጋዊ በርሀ(በሪሁ)ሌሎችም ኣያነሳቸውም።ሁሉም ነገር ይኑሩ ኣይኑሩ ኣሁን በስልጣን ላሉ የህወሓት መሪዎች የሚያጎላ ነው።ቀውስ ፈጣሪዎች ሲነቃባቸው በያዘው ያዘው የተያዙ ሳይሆን እነሱን በማሳመን ስብሰባ ተደርጎ በሂስ ግለሂስ ነው የተፈታ።በፊልሙ ያለው ፍፁመ ትክክል ኣይደለም።እንዲያውም ያ የነበረ የግጭት ኣፈታት ህወሓት በዲሞክራሲያዊ ኣፈታት ሲታይ ኋላ ኣሁንም ያልታየ ነው።

ኣለማዮህ ኣየለ(ድራር) ይዟቸው የከዳ 5 ታጋዮች ሙሴ በጠላት እጅ እንደወደቀ እነዛ ሙሴን ለማስወጣት ሽሬ የሄዱት ለሙሴ ካስወጡ በኋላ ነው።እነ ተፈራ ታደሰ የተሰናበቱት ሙሴ

ካወጣን በዊዳክ ኣከባቢ ነው።ቀውሲ ፈጣሪዎች ተብለው ታስረው ያየናቸው በወቅቱ በገመድ ይሁን በሌላ የታሰረ ኣልነበረም።እዚህ ላይ ሰዎች በጨርቅ ታስረው ያሳዩን ስህተት ነው።ህገ ደንብ ህወሓት የፀደቀው ሙሴ ከተፈታ በኋላ በነሃሴ ኣጋማሽ በዕዳጋ ባርያ መረብ ኣከባቢ ነው።ያ በሙሴ የቀረበ ህገ ደንባችን ሰው ገዳይ ኣይደለም የሚል ቃል ውሸት ነው ኣልነበረም ኣልተናገረም።የኦፕሬሽኑ ስም ሙሴ መሆን ኣልነበረበትም ።ኦፕሬሽን የተካሄደው ሙሴ ለማስወጣትና የመጀመርያ የህወሓት ኦፕሬሽን ነው ስለሆነ የመጀመርያ ኦፕሬሽን ሽረ መሆን ነበረበት።

ሙሴ ለማውጣት የተጓዙ ታጋዮች ከየት ተነሱ በጉዛቸው ያጋጠማቸው ችግር ምን እየበሉ በመንገድ የሚተባበሯቸው ሰዎች ነበሩ ወይ?የኣየር ፀባይ ስንቃቸው ወዘተ.ኣይገልፅም።

በገጠርም በከተማ የነበሩ የህቡእ ድርጅት ሚና ኣይገልፅም።በኦፕሬሽኑ ወሳኝ ኣስተዋፅኦ የነበራቸው ከገበሬዎች ይብራህ ትርፉነህ ከእንጎይላ ከኣስገደ ገ/ሃንስ ገብረሴት፣ገ/ሂወት ገብረሴት ከክሳድ ጋባ ኣስገደ የይብራህ ትርፍነ እህት ከፃዕዳ እባ ኣስገደ ይህሉፍ እህት ከፅንብላ ጭደራ።

ከከተማ ዮውሃላሸት መለስ ኣሁን ናዝሬት ያለው ኣማሃይ ኣብረሀት ሃጎስ ወይዘሮ ዘውዱ ልጆቻቸው በሪሁ ፣ኣፈወርቅ፣ብርጭቆ ሊባኖስ፣በርሀ ካህሳይ ስዩም ከሽሬ ወዘተ.ኣልተጠቀሱም።ለሙሴ ለማስወጣት ኦፕሬሽኑ 2 ግዜ ሳይሳካ ተደናቅፏል በፊልሙ ግን ኣያሳይም፤ያን ቢታይ ኖሮ ለፊልሙ ሂዎት በሰጠው ነበር።

ያቡድን ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ ወታደራዊ ኣዛዥ ሆኖ የሚመራው የነበረ የሜዳ ስሙ በሪሁ ዋና ስሙ ኣረጋዊ በርሄ(በኣሁኑ ደጉተር ኣረጋዊ) በውጭ የሚኖር ነው።በፊልሙ ግን መሪም ሰላይም ኣድርጎ የሚቀርበው ስዩም መስፍን ነው ለምን?ስዩም መስፍን ስለላው በትክክል ሰርቷል ጀግና ነው በፊልሙ ግን ኣግዳሚያው ሲጎት ውሃ ተነክሮ ሲታጠብ ታይቷል ይህ ኣልነበረም ተጋንኖዋል።

ወደ ጣብያ ሲገባ ቦምባ ቻይና የጣለ ስዩም ይታያል ሃቁን ግን ወደፊት ታስቤ ገብቼ ቦምባ ቻይናን የተኮስኩት እሱር ቤት የተቆጣጠርኩት እኔው ኣስገደ ነበርኩ።ስዩም መስፍንም ቦምባ ኤፍዎን በመተኮስ በስተቀኝ የነበረ ዘበኛ በመምታት ጅግንነት በተሞላው ስራ ሰርቷል።ኣሁንም ግን ወታደራዊ መሪ ኣልነበረም።ስዩም የራሱ ጀግንነት ኣይበቃውም ነበርን?ታድያ ለምን ለስዩም የራሱም የሌሎችም ጀግንነት ተሰጠው?

በኣጠቃላይ በኦፕሬሽኑ ስራ ጎልቶ የሚታይ የስዩም ነው።ሌሎች እንደነ ቀለበት፣ተክለ ሽሪፎ፣ኣረጋዊ በርሀ፣ኣግኣዚ እና ራሴ ኣስገደ ኣንታይም?ኣሕፈሮም ይነሳ ነበር ግን ኣልነበረም።

ለሙሴ ብቻየን ከእስርቤት ኣስወጥቼ በግምት 100ሜትር ተሸክሜ እንደሄድኩ ወደቅኩና ስዩም መስፍን ኋላ ቀርቶ ጨርሰናል የሚል የቦምብ ተኩሰ ምልክት ተኩሶ ደርሶ ለሙሴ ተሸክሞት ሄደ ለኔም ደክተር ኣረጋዊ በርሄ በእጁ ኣንጠልጥሎ ደግፎ ወሰደኝ፤ሁኔታው ይህ እያለ በፊልሙ ጎልቶ ኣይታይም።እዚህ ላይ ፊልሙ ኣድርባይና ጌታ ኣዳሪ ፊልም በዚህም ፊልም ሁሉም ነገር ስዩም እንደሰራው ያሳያል።

ደግሞ ሙሴ ስናስወጣው እሱ ብቻ ኣልነበረም ከ50 በላይ ከሱ ጋር ነበሩ በሌላ ክፍልም ከ70 በላይ ነበሩ ከነዚህ ውስጥ የኛ ኣባል ኣያሌው ስዩም እዛ ውስጥ ነበረ ግን እነሱ ሁሉም ከሙሴ ጋር ተፈቷል።በተጨማሪ መሙሴ ከተያዘበት እስከወጣበት ጀምሮ ለብቻው ታስሮ ኣያውቅም ለምርመራና ምግብ ለመብላት ብቻ ወደ ፖሊስ ፅ/ቤት ይወጣ ነበር።ፊልሙ ይህ ኣያሳይም።

ሙሴ በእሱር እያለ ለፖሊስ ኣዛዦች ያታልላቸው እንደነበረ ብዙም ባይሆንም ፊልሙ ኣሳይቷል።የፖሊሶቸ ዲሞክራሲያዊ ኣቀራረብ ግን እንደሱ ኣልነበረም ያስፈራሩት ነበር መግረፍ ጀምረውት ነበር።

ሙሴ በኣውቶቡስ መቀሌ ሊሄድ ነው ከተሰማ በሪሁ፣ኣግኣዚ፣ቀለበት ኣብረው ተሳፍረው ሂደው በመንገድ ሊያወርዱት(ሊገድሉት)ከፖሊስ ቀምተው ሊወስዱት እቅድ ወጥቶ ነበር።ይህ ኣልተካተተም ምክንያቱም ትልቅ ስራና መስዋእት የሚጠይቅ እቅድ ነበር።

የሽሬ ፖሊስ ጣብያ ዙሪያው ግንብ ኣልነበረም በባህር ዛፍ ኣጥርና በኣንድ በኩልም ቆርቆሮ ነበረው በፊልም የሚታየው ግንብ ነው።ይህም ስህተት ነው።
የሙሴ ኦፕሬሽን ለመፈፀም የተጓዘ ቡድን ከተነሳበት ጀምሮ ሙሴ እስከወጣ ከዛን በኋላ የማያቋርጥ ዝናብና ጉም ወንዞች ሞልተው ለጉዞ ኣስቸጋሪና ረሃብና ብርድ እንደነበር ፊልሙ ኣያሳይም ግን ይህ ዋና የፊልሙ ሂወት ነበር።
በፖሊስ ጣብያ የነበሩ ከ6 እስከ 8 ፖሊሶቸ ነው የነበሩ ።በሽሬ ኣንድ ሺ ወታደር ኣልነበረም።የሽሬ ህዝብ ግን ከ1000 በላይ በየቤቱ ህቡእና ፍቃድ የነበራቸው ብረቶቸ ነበሩት በዛ ወቅት ሁሉም ብረቱ በተኩስ ሞክሯል።ፖሊስ ነጭ ለባሽ የእስር ቤት ፖሊሶችም ግን በመቶ የሚቆጠሩ ነበሩ።
ሌላ ፊልሙ ሙሴ ከወጣ በኋላ ወዴት ሄዱ ምን ችግር ኣጋጠማቸው በህዝብ የተደረገላቸው ትብብር ኣይገልፅም።ምክንያቱም ሙሴ ይዘን ከወጣን ጠላት በኣየር ስለላ እያደረገ በሄሎኮፕተር ኩማንዶዎች ከኣስመራ ኣምጥቶ ያድነን ነበር ህዝብ ግን ደብቆናል።
በኦፕሬሽኑ እንዳይካፈሉ ወደ ርቁ ቦታ ይዞዋቸው የጠፉ የኣረጋይ ተወልደ(መፍቱሕ) ሴራ ኣልተገበፀም።
ሌላ ሙሴ ፊልም የሚተርክ ከሆነ መጨረሻው ሙሴ የትገባ ስለሆነም ኣሰያየሙ ትክክል ኣይደለም።
ከኦፕሬሽኑ በኋላ ሄለኮፕተሯና የስለላ ኣየር ነበሩ ደርግም ተጨንቆ ነበር ኣልታየም።እነ ሃየሎምና ብርሃነመስቀል የመጡት ኣንደኛ  ሙሴ ከተሳረ ነው ሁለተኛ ይዘውት የነበረ ብረት ግንፅል 6 ጥይት ጎራሽ ነው።ኣፈድስት ጓንዴ ኣልነበረም።ፍስሃ ሜዞን ክልተን በኦፕሬሽኑ ምንም ሚና ኣልነበረውም በፊልሙ ግን ተቀምጧል ለምን?
ሌላ የፊልሙ ኣዘጋጆች እንዴት እንዳዘጋጁት ሲገልፁ ፀጋይ ሃዱሽ 10 ኣመት ሙሉ ጥረት እንዳደረገ ብርሃነ ንጉሴም ለኣመታት እንደሰራ ነው የሚተርኩ።
እንግዲህ ይህ ጉዳይ ህዝብም ይውቅው፤
ፀጋይ ሃዱሽ ከ10 ኣመት በፊት ጋዜጠኝነት ሊመረቅ ማስመረቅያ ፅሑፍ እንዲያዘጋጅ ተነግሮት ፀጋይ ማሞ ከሚባል ጓደኛ  ጋር ቤቴ ድረስ ይመጡ ነበር።እነዚህ ልጆች በትህትና ለመመረቂ ፅሑፍ ስለምናዘጋጅ የሽሬ ኦፕሬሽንና የኣክሱም ኦፕሬሽን ኢንፎርሜሽን ተባበረን ብለውኝ እኔ በወቅቱ ወደ ሩቅ ኣገር ለስራ ይሄድ ስለነበርኩ በቃል ኢንፎረሜሽን ለመስጠት ግዜ ኣልነበረኝም የነበረኝ ኣማራጭ ለልጆች ለማገዝ ስል ኋላ ጋህድ 2 ሆኖ ያሳተምኩት መፅሓፈ ለረጅም ግዜ በእጅ ፅሑፍ ተዘጋጅቶ ስለነበር ለፀጋይ ሓዱሽ 70 ገፅ የሽሬ ኦፕሬሽን ለፀጋይ ማሞ ወደ 90 ገፅ የኣክሱም ኦፕሬሽን ቤቴ ሆነው ገልብጠው እንዲወስዱ ከልጄ ኣያይገቼ ምግብ ሻሂ እንዲሰጣቸው ኣዘዝኩላቸው 2 ቀን ሙሉ ገልብጠው ወሰዱት።ሁለቱም በኔ ፅሑፍ ተመረቁ ኋላ ሁለቱም ፊልም ለመስራት ሓሳብ እንዳላቸው ኣወቅኩ።ፀጋይ ሓዱሽ ኣዲስ ኣበባ ሄደ።ኣንድ ኣንድ ሰዎች ተሰማምቶ እንደነበር ኣውቃለሁ ፀጋይ ግን ስክርቢት ለመስራት 10 ኣመት ፈጀብኝ ብሎ ሲዋሽ ሰማሁ ኣሳዛች ነው ለምን በልጅነቱ የሰው ኣእምሮ ሰርቆ የሰራው 10 ኣመት ሰራሁ ብሎ መዋሸት ጥሩ ታሪክ ኣይሆንም።
በሌላ በኩሉ ብርሃነ ንጉሴም እኔ ኣላውቅም ጋህድ ኣንድና ሁለት መፅሃፎቼ ለህትመት ከበቁ በኋላ ኣንብበዋቸው መሰለኝ፣በስልክ ደውሎ ስለ መፅሓፎቼ ኣድናቆትን ሰጠኝ መቀሌ መጥቶ ሊያገኘኝ እንደሚፈልግ ነገረኝ።ቤት መጣ ተቀበልኩት ኣንድ ቀንም ኣክሱም ሆቴል ኣልጋ ይዞ ስለነበር ጠራኝ ምሳም ጋበዘኝ ፊልም እሰራለሁ ብሎ

ሳይነግረኝ ሽሬ ኦፕሬሽንና ኣክሱም  ኦፕሬሽን በሚመለከት በጥልቀት ይጠይቀኝ ነበር።እኔም ያለ ኣንዳች ልግምት ሰጠሁት።በጋህድ ሁለት ያለው ወፍሪ ሽሬ የሚለው በጥልቀት ነገርኩት።ቆየት ብየ ፊልም ይሰራ እንዳለ ኣወቅኩ ኣሰራሩ ድቡብቀሽ ነበር።ኣሁን ሳየው በግልፅ ቢነግረን ኣግዘው ነበር ግን የሱ ስህተት ኣይመስለኝም።የህወሓት መሪዎች ኣታስጠጋው ብለውት እንደሚሆኑ ኣልጠራጠርም።

እኔ ይህ ታሪክ ለመግለፅ የፈለግኩ ፊልም ለምን ተሰራ ኣይደለም።እኚህ ሰዎች

1.ኢንፎርሜሽኑ ተፈትፍቶ የተሰጣቸው እያለ ያልደከምኩበት ለጉራ ሲሉ ድስኩር ማድረጋቸው ለምን?

2.ፊልማቸው ተቀባይነት እንዲኖረው ምንም የማያውቁ ባለስልጣኖች ዋና ተባባሪዎች ኣድርገው ማስቀመጣቸው ይህ ኣድርባይነታቸው ያረጋግጣል።

3.በፊልሙ ላይ ተሰሚነት ኣላቸውና ገንዘብ ይሰጡናል ሌላ ሌላ ጥቅማጥቅሞች ይሰጡናል ለሚላቸው ያለታሪካቸው በመስጠትና ማጉላት ታይቷል።

የተከበራችሁ ኣንባብያን እኚህ ሰዎች ሃቅነት ቢኖራቸው

1.መቀሌ ቦስተን ሲኒማ ቤት ስለ ኦፕሬሽኑ ምንም እውቅና በሌላቸው ሲገመገም ለኔ ሊጋብዙኝ ኣልቻሉም።ለምን የሚለው እኔ ያየሁትና የማውቀው በተግባርም የነበርኩበት ስለሆነ ሃቁን ልናገር ነው።በኣሁኑ ግዜ ደግሞ ሃቁን የሚናገር ኣይፈለግም።ምህረቱን ይስጠን እንጂ ኣስቀድሜ ኣይቼው ቢሆን ኖሮ ኣሁን የምለው ያለሁት ይስተካከል ነበር።

2.ፊልሙ በመቀሌ ሲመረቅ ከተለያዩ ዞኖች ወረዳዎች የስውኣን ቤተሰቦች ኣካል ጉዳተኞች ግለሰዎች በመቀሌም ብዙ ወደ 1500 በላይ ጥሪ ተደርጎላቸዋል።የሚገርመው ግን እኔ በኦፕሬሽኑ ወሳኝ ሚና የነበረኝ በሂወቴ እያለሁ ኣልጠሩኝም።በምርቃኑ ጉድን ለማየት መካፈል ኣለብኝ ብየ ስለወሰንኩ ጥሪ ከተደረገላቸው ሰዎች ወረቀት ስጡኝ ብየ ገባሁ።ከላይ የዘረዘርኳቸው በፊልሙ ያለው ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ልገመግም ቻልኩ።ለምን እንደሆነ ለምን ያገሉሃል የሚል ጥያቄ ሊመጣ ይችላል።የሚገርማችሁ በህወሓት እያለሁ ለሁሉም ነገር ኣስገደ ስለሚያውቅ ወደ ኣስገደ ሂዱ ነው የሚባሉ የነበረ ኋላ ከህወሓት ወጥቼ በኣስተሳሰብም በፖሊሲም በሁሉም ኣይነት ዲሞክራሲያዊና ሰብኣዊ መብቶች ኣለመከበር ፤በውስጥ ድርጅትና ሌሎች እንደ ኤፈርት ድርጅቶች ዋንነት በሚመለከት ተቃዉሞ ስለማሳይ ኋላም በተቃዋሚ ፖለቲካዊ ፓርት ተሰልፌ በመቃወሜ በሰላማዊ መንገድ ህገ መንግስታችን በማክበር መቃወም ወንጀል ሆኖ የህወሓት መሪዎችና ወደነሱ በጥቅምና በኣላማ የተሳሰሩ ገለልተኛ ያደርጉኛል።እኔ ግን

ታሪኬ ተግባሬ የትግራይ ህዝብና ታጋዮች ስለሚያውቁት ብዙ አልጨነቅበትም።
ወደዱም ጠሉም ከህወሓት ተሰልፎ እስከ ከህወሓት ጋር የምፋታ 1986ዓ.ም ህወሓት የሰራው በጎ ይሁን መጥፎ ታሪክ በዚያች በነበርኩባት ደረጃ ተመስጋኝም ተጠያቂም ነኝ በመታገሌ የሚቆረቁረኝና የሚቆጨኝ ነገር የለም።ያም ስለሆነ የ17 ኣመቱ ታሪክ የምፅፈው ህወሓት ሁኜ እንጂ ዓረና(መድረክ)ሁኜ ኣይደለም።የነበረ ሃቅ እንዳይዛባ ግን ኣሁንም እታገላለሁ።በመጨረሻ ምርቃ የፊልሙ ዳይሬክተር ማጠቃለያ ንግግር ሲያደርጉ ገንዘብን ልመና ማእከል ያደረገ፤ይላሉ ይህ ፊልም በኣማርኛ ቅረፁትና ስፖንሰር እንሰጣችኋለን ብለውናል።እኛ ግን በትግራይ የተሰራ የትግሬዎች ስልሆነ ድህንታችን ይዘን በቋንቋችን ትግርኛ ነው የምንሰራው ብለን ነው በትግርኛ የሰራነው ይላሉ ብርሃኔ ንጉሴ።
ኣሳፋሪ ነው በበኩሌ እቃወማለሁ።በትግርኛ ለምን ተሰራ ኣልልም ጥሩ ነው ግን ደግሞ በትግራይ የተሰራ የትግሬዎች ስለሆነ በትግርኛ ብቻ ይሰራ ማለቱ ኣማርኛ ቢሆንስ የትግራይ ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ ኣይደለም።የኣማራ፣አሮሞ፣ደቡብ፣ሱማል፣ኣፋር፣ጋንቤላ ወዘተ.ታሪክ የኢትዮጵያ ኣይደለም ወይ?በኔ እምነት በመላው ኢትዮጵያ ኣከባቢ የሚገኙ ህዝቦች የሰሩት ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ ነው።ስለዚህ ኣቶ ብርሃኔ ንጉሴ ጠባብነትን ኣያስፈልግዎትም ነበር።ለምን በኣማርኛ ተሰርቶ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ኣያውቀውም ኣለም ሊያውቀው በእንግሊዝኛ ቢሰራ ምን ችግር ኣለው?
ጀማይካ በፊልሙ ውስጥ ከሙሴ መታሰር ብቻ በፊልሙ ሊገባ የሚገባው፤ጀማይካ ከሻዕብያ ሰላይ ሆኖ ወደ ህወሓት የተቀላቀለው ሙሴ ሊያግዝ ለምኖ እንዳመጣው ይገልፃል።ይህ ለምን ገባ?በተጨማሪ ሙሴ ወደ ህወሓት ሊመጣ የቻለ በህዝባዊ ግንባር ለህወሓት በነበራቸው በጎ ኣስተሳሰብ የትግል ተሞክሮ ለህወሓት ለማሰለፍ ለሙሴ በስጦታ እንደ ሰጠ ፊልሙ ይተርካል።ይህስ ምን ኣመጣው ኣዲስ ታሪክ እያገረሸ ነው ያለቦታው ገብቶ።
**መጨረሻ ኣስተያየት**
1.የፊልም መሰራት በጣም ጥሩ ቢሆንም ብዙ ስህተቶች ስላሉት ወደ ህዝብ ከመቅርቡ በፊት የጠራና ታሪክን በማያበላሽ ሃቁን በሚያረጋግጡ ሰዎች ታይቶ ቢሰራ በበኩሌ ያለ ኣንዳች ክፍያ ላግዛችሁ ዝግጁ ነኝ።
2.የፊልሙ ገፀ ባህርያት የሙሴና የስዩም በመጠኑ የተሻለ ካልሆነ በስተቀር የሌሎችም ምንም ኣይመስሉም።
3.ኣሁን ፊልም መስራት እንደምትችሉ ስለታወቃችሁ ስፖንሰር ኣታጡም ሳትሰላቹ ስሩት ካለበለዝያ ይህ ፊልም በህዝቡ እየሰረፀ በሄደ

ቁጥር መጥፎ ስሜትን ይፈጥራል።ሰዎች በግልፅ ባይናገሩም ፊልሙ የተከታተሉ ብዙ ትችት እየሰነዘሩበት ናቸው።
4.ታሪክን ልትወደድ ብላችሁ ኣታበላሹ ስልጣን ተቀያሪ ነው ህዝብ ነዋሪ ነው።
5.በፊልሙ ለኣቶ ስዩም መስፍን የተሰራ ይመስላል።ይህ ደግሞ ለሰራችሁት ፊልም ታማኝነታችሁ ዝቅ ያደርገዋል ስለሆነም ይታረም።
ይህ ኣስተያየት ብትቀበሉት ባትቀበሉት እኔ ግድ የለኝምም ያን ያየሁት ደካማ ጎን በኣጭር ግዜ መልስ(እርማት) ሂስ መስጠቴ ለናንተ ጠቃሚ ስለሚሆን ተሎ ብላችሁ እዩት።
በኣሁኑ ግዜ የህወሓት ታሪክ ለማወቅ ቀላል ስለሆነ ሌሎችም ኣሻሽለው ሊሰሩት ይችላሉ።


በኣስገደ ገ/ስላሴ ወ/ሚካኤል

መቀሌ

ስ.ቁ 0914757242

ኢ. ሜል asgedeg@yahoo.com